__መልስ፡-__

እግዚአብሔር አምላክ በሚፈቅደውና በሚወድደው፥ በሚፈልገውና በሚቀበለው፡ በእርሱ እውነትና በመንፈስ ቅዱስ ከሚፈጸምው አምልኮተ እግዚአብሔር በቀር፡የ፯ሺ፭፻፭ ዓመታት ዕድሜ ባላት፥ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውንም አዋሕዳ በያዘችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሃይማኖትና ምግባር፥ አቋምና ሥርዓት ውስጥ፡ የጣዖትና የጥንቆላ፥ የምስልና የርኩሳን መናፍስት ባዕድ አምልኮ፡ እንኳንስ ሊደረግ፡ ፈጽሞ አይታሰብም።

ጠልሰምም፡ ከእነዚሁ፡ የባዕድ አምልኮ መሣሪያዎች አንዱ ስለኾነ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ጨርሶ ተቀባይነት የለውም። በእ-ጦማርዎ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱት መጻሕፍትም፡ የዲያብሎስ አገልጋዮች የኾኑ "የቤተ ክህነት ወገኖች ነን!" የሚሉ አሳሳቾች፡ ለኃጢአት ሥራ የሚጠቀሙባቸው ሊኾኑ ስለሚችሉ፡ ብርቱ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው፥ በጥንቃቄም ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው። ሕዝቡን በጥንቆላ፥ በሰይጣንና በባዕድ አምልኮ፡ ቀሥፈው ይዘው እንደሚጫቅዩበት፡ "ዐውደ ነገሥት" እንደሚሉት መጽሓፍ ማለት ነው።

እንዲህም ስንል፡ የንሥር ኾነ የሌሎች አዕዋፍ፥ የእንስሳትና የአራዊት፥ ወይም፡ የሰዎች ሥዕሎች፡ ሊኖሩ አይገባም ማለት አይደለም። እኒህ ኹሉ፡ የእግዚአብሔር ፍጡራን ስለኾኑ፡ እንደሰው ሊወደዱና ሊከበሩ ይገባቸዋል። ለዚህም፡ መንበረ ጸባኦትን የሚሸከሙትን አርባዕቱ እንስሳትን፡ በማስረጃነት መጥቀሱ ይበቃል። አኹን ለተነሣንበት፥ አከራካሪና አጠያያቂ ለኾነው፡ ዋና ርእስ ግን፡ መልስ የሚኾነው ቁም ነገር፡ የጠልሰሙንም ኾነ ሌላውን ሥዕልና ጽሑፍ፡ የአምልኮ ምልክት አድርገን እንዳንጠቀምባቸው፡ እጅግ በጣሙን መጠንቀቅ እንዳለብን ማስገንዘብን ነው።

"ጠልሰም" ተብሎ፡ በግእዝና በኢትዮጵያኛ (በዐማርኛ) የሚነገረውን ይህን ቃል፡ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ ግእዙን፡ "ክታብ፤ ጠንቋዮች፡ በጥቁር ቀለም ጥፈው (ጠልስመው)፡ የሚያሲዙት። ክታብ፡ አስማቱ (የጥንቆላው ቃላት)፤ ጠልሰም፡ በያስማቱ ውስጥ የሚጣል፡ ሥዕልና ሓረግ፥ ሡንጠረዥ፥ ሙጭርጭር ጥፈት ነው።" ብለው ሲፈቱት፡ ኢትዮጵያኛውን ደግሞ፡ ደስታ ተክለ ወልድ፡ "ጠለሳም፤ ባለጠለስ፤ በያይነቱ፡ ያስማት ሥዕል፤ ለራስ ምታት፣ ለሆድ ቍርጠት፥ ለውጋት፥ ለቍርጥማት፡ በክታብ ውስጥ፡ ጠንቋዮች የሚሥሉት። እስላሞች፡ ባንገታቸው የሚያደርጉት፡ የብር፥ ወይም፡ የወርቅ ዐሸን ክታብ።" ብለው ተርጉመውታል።